የረቡዕ ጥር 9 ቀን 1999 ዓም( ጃንዋሪ 17 2007)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ ሐተታ

### ኢትዮጵያ ዘለዓለም ዕጓለ ምውታን ሆና አትቀርም

በዛሪይቱ ዓለማችን፥ በተፈጥሮም ይሁን በሰው-ሰራሽ ምክንያቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናት ወላጆች አልባ ሆነዋል፡፡ እነኝህ ህፃናት በምን ሁኔታ ላይ እንደሚኖሩ ሊሰማውና ሊረዳው የሚችለው ደግሞ በተመሳሳይ የዕደገት ሂደት ያለፈና ለአካለ-መጠን የደረሰ ዓዋቂ ሰው ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የእናትና የአባት ፍቅር ተነፍጎት ያደገ ህፃን፥ እንደምንም ብሎ ለአካለ መጠን ከደረሰ፥ በኋላ ላይ በህብረተሰብ ውስጥ የሚያደረሰው፥ የሚያመጣውና የሚጫወተውን ሚና በትክክል ሊያውቁት የሚችሉ የሥነ አዕምሮና የሥነ ልቦና ጠበብት ብቻ ይመስሉናል፡፡ እንዲያው በደፈናው፥ የወላጆች ፍቅር ተነፍጎት ያደገ ህፃን፥ ያስተዳደጉ ሁኔታ ጥሎበት የሚሄደው የልብና የአዕምሮ ጠባሳ እንዲሁ በቀላሉ የሚሽርለት አይሆንም፡፡ ፍቅርና እንክብካቤ ተነፍጎት ያደገን ሰው፥ የማያውቅውን፥ በህፃንነቱም ያላየውንና ያልተሰጠውን ፍቅር አሳይ ቢባል፥ " ከየትና ከማን ያላገኘሁትን ፍቅር ከወዴት አባቴ ላምጣው?" ብሎ ቢጠይቅ፥ ኅብረተሰቡ መልስ መስጠት የሚቸገረው ይመስለናል፡፡ ዕጓለ ምውታን የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ ሰለባዎች ናቸው፡፡ የተፈጥሮን ፍረደ-ገምድለንት ምንም ለማድርግ ባይቻልም፥ የኅብረተስብን ግዴለሽነትና ጭካኔ ግን ቢቻል ማሰወገድ ካልተቻለ ደግሞ መቋቋም ይገባል፡፡ ይህ ካልተደረገ የአንድ ሀገር ሥነ ልቦና አንድ ዕፀፅ አለበት ማለት ነው፡፡ ያ ደግሞ ሰፋ ተደርጎ ሲገመገም፥ በአንድ ሀገር ሕዝብ ላይ የሚያመጣው ጫና ቀላል አይሆንም፡፡

ዕጓለ ምውታን መሆን፥ በህፃናት ላይ ተወስኖ የሚቀር ክስተት አይደለም፡፡ ሀገርም እንደ ሰው ልጅ ዕጓለ ምውታን የሚሆንበት አያሌ የታሪክ አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ለዚህ እንደ ህያው ምስክርና እንደ ተጨባጭ ምሳሌ የምትጠቀሰው፥ ያው ያችው መከረኛዋ የኛይቱ ሀገር ኢትዮጵያ ነች፡፡ ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የሚያዝንላት ባዕድ ቀርቶ የራሷ የሆነ መንግሥት እንኳ አጥታለች፡፡ ይህም በመሆኑ፥ በታሪኳ ገጥሟት የማያውቅ በደልና ጥቃት ሲፈፀምባት፥ ዳር ድንበሯ ሲደፈርባት፥ ዕልፍ አዕላፍ ልጆቿ ሲጨፈጨፉባት፥ በርካታ ዜጎቿ እንበለ-ፍርድ በወህኒ ሲማቅቁባት፥ በአያሌ ሽ የሚገመቱ ልጆቿም መዳረሻቸው ያልታወቀ ሆነውባት፥ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ሲሰደዱባት፥ በርካታ ሴት ልጇቿ በየዐረብ ሀገሮች ሲጎሳቆሉባት፥ ሲዋረዱባት፥ የኃይማኖት አባቶችና ምዕመናን ቤተ መቅደስና መስጊዶቿን እየዘጉ ከሀገር ሲወጡባት፥ ቆሞ የሚከላከልላት ማግኘት አልቻለችም፡፡ በዚህ ምክንያት፥ እናት ሀገራቸውን በመጥላት ሳይሆን፥በሀገራቸው ምድር መኖር ስላቃታቸው ብቻ፥ ዛሬ ዜጎቿ የመጀመሪያው ምርጫቸው ሀገር እየለቀቁ መሰደድ ሆኗል፡፡

ይህ በሀገርና በሕዝብ የሚፈፀመው በደልና ውርደት ያለማቋረጥ የሚካሄደው፥ ኢትዮጵያን የሚታደጋት ተቆርቋሪ ስለሌላት ብቻ ነው:: ወላጅ የሌላት፥ ጥቃቷን የሚመክትላትና በደሏን የሚያስወግድላት ያጣች ሀገርም በመሆኗ ዕጣ ፈንታዋ ልክ የዕጓለ ምውታን ዕድል ሆኗል:: ይህ ሁሉ አልበቃትም ተብሎ ፥ ለዘመናት አብረው በሰላምና በኅብረት እየኖሩ፥ የውስጥ ጭቆናውንም ይሁን፥ የውጭ ወረራውን በመተባባር የተቋቋሙትን ዜጎቿን፥ በዘርና በቋንቋ እየተከፋፈሉ ተለያይተው እንዲኖሩ እየተገፉ ነው:: ይህ ሁሉ የሚደረገው፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለብሄራዊ ጥቅሟ፥ ለነፃነት ልዕልናዋ፥ ለሀገራዊ ክብሯ፥ ለሕዝቧ ደኅንነትና ብልፅግና የቆመ መንግሥት ባለማግኘቷ ብቻ ነው:: ለሀገርና ሕዝብ የቆመ መንግሥት ከሌለ ደግሞ፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፥ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ መኖር ቀርቶ መቆየት እንደማይችሉ ይኸው ዛሬ እየታየ ነው::

አሁን እምኒልክ ግቢ ውስጥ የመሸጉት የአንድ ብሄር ድርጅት ቡድኖች፥ ማንነትና ምንነት በኢትዮጵያ ሕዝብና በመላው ዓለም የታወቀ ስለሆነ፥ በዚሁ ላይ በማተኮርና ስለእነኝህ ሀገር አጥፊ ግለሰቦች ጊዜ ማጥፋት፥ እራሱ ሥራ መፍታት ነው የሚሆነው:: ከዚህም በቀር፥እነርሱ እራሳቸውም ቢሆኑ፥ የኢትዮጵያን ጥፋት የሚፈጽሙት፥ ዓለም እያወቃቸው፥ ፀሀይ እየሞቃቸው ስለሆነ፥ እናም ደግሞ፥ ለአለፉት አስራ ስድስት ዓመታት የነመለስ ዜናዊን ብሄራዊ ወንጀል በሁለንተናዊ ገጽታው ተመዝግቦ የተቀመጠ ስለሆነ፥ ኢትዮጵያ የራሷን ጥቅም የሚያስጠብቅላት መንግሥት ባለመኖሩ የሚያስደንቅ አይሆንም:: በመንግሥት በኩል ኢትዮጵያና ዜጎቿ ዕጓለ ምውታን ናቸው ቢባልም፥ ያን ያህል ሊያስገርም አይችልም:: ስለዚህ ብሔራዊ መንግሥት አልባ የሆነች ሀገር መሆኗ ከታወቀ ፥ ብሔራዊ ጥቅሟን ሊያስጠብቅላትና ከእጓለ ምውታንነት ሊያወጣት የሚችል ማን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፥ ሁሉም ዜጎቿ ሊረባረቡ ይገባል እንላለን:: በአሁኑ ወቅት የመንግሥት ሥልጣን ይዣለሁ የሚለውን የብሔረሰብ ድርጅት ለመለወጥ የሚደረገው ሀገር አቀፍ ትግል እንደተጠበቀ ሆኖ፥ እስከዚያው ድረስ ግን <u>የጋራ ብሔራዊ አጀንዳ ኖሮ፥ ሌላው ቢቀር ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጥቅም የቆመ የጋራ ድምፅ አሰሚ ኃይል መኖር በተገባ ነበር:: ያ ግን አልሆነም:: ይህን ላለማድረግ ደግሞ ማንንም ማውቀስና በማንም ማመካኘት አይቻልም:: ይህ ባለመፈፀሙ ዓይነተኛ ተጠያቂዎቹ እኛው ራሳችን ሁላችንም ዜጎቿ ብቻ ነን::</u>

በአሁኑ ወቅት፥ የመንግሥት ሥልጣንን ተረክቦ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ብሄራዊ ጥቅም መቆም ባይቻልም፥ የነመለስ ዜናዊ ቡድን ኃይለኛ ተቃዋሚ በመሆን የሀገሪቱ ጠበቃና አለኝታ ሆኖ፥ በመተባባር የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ማስከበርና ማስጠበቅ በግድ ያስፈልጋል ነበር:: ይህም ዕውነታ፥ ሌላው ቢቀር፥ ኢትዮጵያንም ዕጓለ ምውታን ከመሆን ያድናትም ነበር:: <u>ኢትዮጵያ አለኝታ አላት:: ተቆርቋሪ አላት:: ሀገራዊ ጥቅሟንና ህልውናዋን፥ በአደባባይ ብቻ ሳይሆን፥ በደሙ ጭምር የሚያስከብርላት ኃይል አለ! ማለት ካልተቻለ፥ ሀገራችን የነመለስና የበላይ ጠባቂዎቻቸው መጫዎቻ መሆኗ ይቀጥላል</u>::

ማነኛውም ሀገር ቅድሚያ ስጥቶ የሚሰራው፥ ያው ለራሱ ሀገር ብሔራዊ ጥቅም እንደመሆኑ፤ በዚህ አደገኛ የታሪክ ሂደት የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚተባበር የውጭ ኃይል ይኖራል ብሎ ማሰብ፥ የዓለም አቀፍን ግንኙነትና ባኅርይን እንዲሁም የዲፕሎማሲን ተፈጥሮና አሰራር በትክክል አለመገንዘብ ይመስለናል። የሌላውን ሀገር ባናውቅም፥ ኢትዮጵያ ግን በታሪኳ የባዕዳን ተጠቂ እንጅ ተጠቃሚ የሆነችበት አጋጣሚ ትዝ አይለንም። በዕርግጥ በዚህ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት፥ ሀገሮች የሚቀራረቡበትና ዕርስ በዕርስ የሚጠቃቀሙበት ክስተት በሰፊው የተዘረጋ በመሆኑ፥ ሀገራችንም ከዚህ ክስተት ክልል ውጭ ልትሆን አትችልም ይሆናል። እንዲያውም፥ ከዓለም አቀፍ የሀገሮች ግንኙነትና የዲሎማቲክ ክበብም ውጭ ልትሆን አትችልም። አይገባትምም። ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት በተራራዎቿ ተከብባ በብቸኝነት የኖረችበት ዘመን ይበቃታል። ይህ ማለት ግን እንደነ መለስ ዜናዊ የባዕዳን ጥቅም አስጠባቂና አገልጋይ አሽከሮች የሆኑ መሪዎች ይኑራት ማለት አይደለም። የሀገር አኩሪና አለኝታ መሪዎች እስከሚመጡ ድረስ ሀገራችንን፥ ባዕዳን በወኪሎቻቸው በነመለስ ጋሻጃግሬነት እንደፈለጓት የሚጫወቱባትና የሚፈነጩባት ሀገር መሆኗ ይቀጥላል። ይህ ሁኔታ በውድም ይሁን በግድ መቆም አለበት። ያሁኑ የሀገራችን ሁኔታ መለወጥም አለበት።

ዕውነቱን እየተናገርን፥ ሀቁን እየመሰከርን "በመሸበት ማደር"፥ ባኅርያችንና መለያችን ከሆነ፥ ዕውነቱን፥ ለምንታገልለት ሕዝብ ማሰማታችንን እንቀጥልበታለን። የወቅቱን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስንታዘብ፥ ብሩኅ ተስፋ የሚሰጥ መሠረታዊ ዕውነታን እንገነዘባለን። ይህም ዕውነታ፥ ዘመን የማይሽረው፥ ወቅታዊው የፖሊቲካ ተፅዕኖ የማያደበዝዘውና የማነኛቸውም ተፈራራቂ አምባገነኖች ጭቆና የማይበግረው፥ የማያንበረክከው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት ትግልና አሸናፊነት ነው። ይህ ክስተት በማያወላውል ሁኔታ፥ በስድሳ ስድስቱ የካቲት ሕዝባዊ አመጽ፤ እንዲሁም፥ አረመኔውን ደርግ ለመጣል በተካሄደው ቆራጥ ታሪካዊ ትግልና በዘጠና ሰባቱ ግንቦት ምርጫ በአንፀባራቂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ምዕራፍ ተመዝግቧል። ይህንን የታሪክ ምዕራፍ አምባገነኖችና የውጭ ጠላቶች ማንበብ ቀርቶ መስማትም ቢሆን አይፈልጉም። ምክንያቱ ግልፅ ነው። ይህንን ሕዝባዊ አመፅ ሲያስቡት ስለሚያርበተብታቸውና አይቀሬነቱም ስለሚያቃዣቸው ብቻ ነው ። ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት አይቀሬ ነው። የታሪክ ሀቅ ነውና!

ይህ ዘመን የማይሽረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት ትግል አቸናፊነትና አይቀሬነት ዕምነታችንን አፅንቶልን የትግላችንን ራዕይ ብሩኅ ቢያደርግልንም፥ የተቃዋሚው ጎራ ያለበት የወቅቱ ሁኔታ ግን "እየፈጩ ጥሬ" ሆኗል። ሁሉንም ያካተተ ጠንካራ የተቃዋሚ ጎራ ፈጥሮ ሀገሪቱን ከዕጓለ ምውታንነት ማውጣት ቀርቶ፥ እየተሰነጣጠቀ መከፋፈል ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማያቋርጥ ስቆቃ ሆኖበታል። እያንዳንዱ ዜጋና የተቃዋሚ ድርጅት ሁሉ ይህንን ሁኔታ በአስቸኳይ ለመለወጥ አዲስ ሁኔታን መፍጠር አንገብጋቢ

መሆኑን መረዳት ያስፈልገዋል፡፡ ኢትዮጵያን ከአምባገነኖች አገዛዝ ለማውጣት አስቀድሞ ጠንካራ የተቃዋሚ ድርጅት ኅብረት መኖር የወቅቱ ተቀዳሚ አጀንዳ መሆን እንዳለበት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቦታው የሚያሰማው ብሄራዊ ዋይታና ሮሮ ሆኗል፡፡ ተስፋ መቁረጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባኅርይ ባይሆንም፥ አሁን ባለው አያያዝ፥ የኢትዮጵያን አስጊና አደገኛ ሁኔታ ለመለወጥ ይቻላል ለማለት የሚደፍር ያለ አይመስልም፡፡ ይህ አባባል፥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለመዳሰስ እንዲረዳ እንጅ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የመጨረሻ አቸናፊነት የሚያመጣው አንዳችም ለውጥ አይኖርም፡፡ ይህን ከተገነዘብን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

በእኛ ዕምነት፥ ታማኝነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሀገሩ የሰጠ ማንኛውም ተቃዋሚ ድርጅትና ዜጋ፥ በአሁኑ ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አለበት እንላለን፡፡

1. እስካሁን የተቃዋሚ ድርጅቶችን ጠንካራ ኅብረት ለመፍጠር የተደረገው ጥረትና መስዋዕት ከንቱ ድካም ነው ባይባልም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠብቀውን ዉጤት አስመዝግቦ ኢትዮጵያን ከዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ማውጣት አልቻለም፡፡ ይህንን ሀቅ መቀበል፥ ስህተትን ለማረምና አዲስ የኅብረት ግንባታ ምዕራፍ ለመክፈት የመጀመሪያው ርምጃ ነው እንላለን፡፡ ስህተተን ተቀብሎ ለዕርምት መዘጋጀት ጠንካራነትና ብልኅነት እንጅ ድክመትና ስህተት አይደለም፡፡

2. የተቃዋሚ ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው መጠላለፍ ብቻ ሳይሆን፥ እያንዳንዱ ድርጅትም ቢሆን የየውስጥ መከፋፍለን በአስቸኳይ ማቆም ይኖርበታል፡፡ ይህ የድብብቆሽና የአይጥና ድመት ጨዋታ የትም እንዳላደረሰ፥ በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ግልፅ ሆኖለታል፡፡ በማንነት ደረጃም ቢሆን ድርጅቶቹ ማን ምን እንደሆነ እርስ በእርሳቸው ተዋውቀዋል፡፡ አንዱ ሌላውን ለማጣጣል የሚያደርገው ሙከራ ሁሉ፥ ከትዝብት በቀር ያስገኘው ውጤት የለም፡፡ በአሉታዊ ማጠየቂያዎች ላይ የሚመሰረት ትብብርም መጨረሻው አላማመሩ በየጊዜው የታየ ነው፡፡

3. አንዱ በሌላው ላይ ጣት እየተቀሳሰሩ ጊዜን ከማጥፋት ይልቅ፥ ሁሉም ወደ አዕምሮውና ልቡናው ተመልሶ፥ ከጥላቻና ከበቀል ራሱን አፅድቶ፥ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በሁለንተናዊ ገፅታው መርምሮ ተንትኖ፥ ሁሉንም ያካተተ ብሔራዊ ጉባዔ ለመጥራት መስማማትና ለተግባራዊነቱም ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት፡፡ ወቅታዊውን የኢትዮጵያን የፖሊቲካ መልከዐ-ምድር በሚገባ ለተመለከተው ዜጋ፥ በተቃዋሚው ጎራ በኩል ዛሬም እንደ ትላንቱ አንድ የትግል ክፍተት እንዳለ ይገነዘባል፡፡ ይኸውም ጠንካራ የተቃዋሚ ጎራ አለመኖር ነው፡፡ ይኸ ክፍተት በአስቸኳይ መሞላት አለበት፡፡ ይህንን ማድረግ ደግሞ ይዋል-ይደር የሚባልለት አይሆንም፡፡ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል ባለመኖሩ፥ የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ የመጡት የአንድ

ብሔረሰብ አባላት ጠባቦች፥ ከበላይ ጠባቂዎቻቸው ጋር በመተባበር፥ ሀገራችንን ዕጓለ- ምውታን አድርገዋታል።

4. በመሆኑም፥ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግር ለመፍታት ትግልን በሁለገብ መልኩ ማፋፋም ሲገባ የመጀመሪያው ርምጃ ሁሉንም ያሳተፈ ብሄራዊ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት ነው። ይህ ደግሞ የሀገሪቱንም መሠረታዊ ችግር ለመፍታት የመጀመሪያው ምዕራፍ ከፋች ይሆናል።